ግንቦት 18 ቀን 2002 ዓ.ም

# ነገርዬው አለቀ እንዴ?

ከአያልነሽ

ተመሥገን። በቃ አሁን ወደ ቅጥቃጤያችን በ"**ሠላማዊ መንገድ**" ተሸጋገረን። ያ "**የጠበበው ምህዳርም**" ሥራውን አገባዶ ጨርሶ፣ ተከረቸመ አሉኝ ። በጄ! ከዚያስ? ከዚያማ ሰውየው በድፍን አገሩ ተመርጥኩኝ ብሎ አዋጀ መንገሩንና ማስነገሩን በሳቅ እየተንከተከትኩ ሰማሁ፣ ተመለከትኩ፣ አንበብኩ። ምን እናድርግ እንግዲህ። ሁሉንም መስማት! መስማት! መስማት ነው ጆሮ አጥር የለው።! እሺ... ለመሆኑ ኦባማ ምን አሉ? ወ/ሮ መርከልስ? የእንግሊዙስ...? ሰውዬው ብርቱ ጓደኛዬ ነው ያለው ሣርኮዝስ?.... ቤልጀም፣ ሆላንድ፣ ስዊድን፣ ዴንማርክ፣ ኖርዌይ፣ ጣሊያን...ወዘተ ጉዳቸው ፈላ! ይሄ ሰውዬ ሳያስቡት የማይሆን ነገረ ያደረገ መሰለኝ ቅምጥሉ ልጃቸው። ደግ ነገር! አሁን ነው አሁን ገና የእውነቱንና የምናውቀውን ባህሪውን ገልጦ ያመጣባቸው። ውኃ በላኝ! እኔ የለሁበትም። አሁን፣ አሁንማ የኦባማን ቁጣ ማየት አልፈልግም። ሰውየው ግን ምን ነካው? አንድ ሰው የቡግናውን "ሦስተኛ መንገድ" እንኳን አያስገባም እንዴ ትንሽ ሽፍንፍን፣ ሽፍንፈን ለማድረግ። 99.9%...? አይመስለኝም! ይህንን እንኳ መቀበል ይችግራል። ቆይ! ቆይ ቆይ! ቆይ ለገሠ ዜናዊ ግን ከስህተቴ ተምሬያለሁ ያለ መሰለኝ። ታዲያ ከስህተቱ ከተማረ የወንድሙን የኢሳያስን ስህተት መድገም አለበት? ለእኔ አይመሰለኝም። ቢያንስ፣ ቢያንስ 90% አድርጎ ሚጢጢ "ቀዳዳ" ቢተው ምን አለበት አለሙ ቶጋ እንኳን ጠረጴዛ መደብደቡን ሊያቆም ነው ማለት ነው....ሃ! ሃ! ሃ ሃ!። አይ! ይሄማ አይሆንም ፈጠጠ እኮ! ወ/ሮ መርከለም ይሄንን የገጠጠ፣ ያፈጠጠ ነገር መመልከት ( ትንሽ ሸፈን ካላደረገላቸው) ትዕግሥታቸውን የሚፈታተን መሰለኝ። ያን ሁሉ ገንዘብ እያፈሰሱ አምባገነንነቱን ካልሸፈነባትማ ሒሳብ እናወራርድ ሳይሉ አይቀሩም። ደግሞ እንዴት ቢጠግብ ነው ሳይሉትም አይቀሩ (በሆዳቸው) ይሄን ሞልቃቃ ልጃቸውን? ችግሩ ደግሞ እኛ "አክራሪዎቹ" ስላለን እንደልባቸው ጮክ ብለው እንዳይቆጡት እኛ የምንሰማባቸው ሆነባቸው ነገራቸውን! ታዲያ ምን ተሻለ? ኡምምምምም። ወይ ዕዳ መግባት። እግዚኦ! አቤት! አቤት! አቤት! ያሰኛል። እንዴት ነው እንዲህ አሳዳጊዎቹን የሚያሳፍራቸውና የሚያሸማቅቃቸው ይሄ ዋልጌ ልጅ - ይች ናት ጨዋታ!

19 ዓመት ሙሉ፣ ሸፍንፍን ድብቅብቅ እያደረጉለት፣ ገንዘባቸውን በማፍሰስ ሲያቀማጥሉት የኖሩት ሞልቃቃ ልጃቸው፣ ባላሰቡትና ባልጠበቁት ሁኔታ ጢማቸው ዱብ እንዲል ነው ያደረጋቸው። ዛሬ እውነተኛውንና ገንዘቡ የሆነ ባህሪውን በሰለሞን ተካልኝ ማርሽ አጅቦ፣ በብራና ላይ ሁሉ ሳይቀር ፎቶውን አስሎና አሰቅሎ ዕርቃኑን በአደባባይ ላይ እናስ ምን ትሆኑ? በማለት ከተፍ ብሎባቸዋል። አሁን አሁን አስቀያሚ ባህሪውን እንካችሁ ብሎ ነው ፊት ለፊታቸው መጥቶ የተገተረው። መጥኔ ለአውሮፓ ሕብረት! መጥኔ ለኦባማ! አሁን ነው የኦባማን ፊት ማየትና መመልከት -ፑፍፍፍፍፍፍ

የዜናዊ ልጅ ዛሬም እንደ 1977ቱ ርኃብ፣ ቅንቡላ የገዛበተን ዶላር፣ የተራበውን የትግራይ ህዝብ ሆድ ነው የሞላሁበት ብሎና ብለው አይኑንና አይናችውን በጨው አጥበው የቀጠፉትንና የዋሹትን ውሸት፣ ዶላሩን ላፈሰሱለት አሳዳጊዎቹ "አሞኘናቸው" በማለት እንደተሳለቁባቸውና እንደተሳለቀው፣ አሁንም "አሞኘኋቸው" ሊለን ከጅሎ ከሆነ...አላማረበትምና እረ እንደሚሆን፣ እንደሚሆን ሁን ብለን መምከራችን አልቀረም። **ማን ላይ ቆመሽ እግዜርን ታሚያለሽ** አሉ። የአራዳ ልጆች እንዲህ ያለውን የዋልጌ ጨዋታ"ፈጣጣ" ይሉታል። ለገሠ ዜናዊ በራሱ ዕብሪትና ድንቁርና መርቅኖ ያለእኔ "**አዋቂ፣ ቀልደኛ(ጆከር)፣ ብልጥ፣**" አልተፈጠረም፣ አልተገኘም ባይ ሆኗልና ዓለምን በሙሉ እያሞኘሁ፣ እየቀለድኩበት ነው ብሎ ምሎ ተፈጥሟል፤ አቤት ልቢቱ።

"በብልጥነቴም" ፈረንጆችን በሙሉ በቁጥጥሬ ሥር አደርጌያቸዋለሁ ብሎም ይገበዛል፣ ራሱንም ያሞኛል። እንዲህ ዓይነቱ ባህሪ የአምባገነኖች ዓይነተኛና ሁነኛ መታወቂያቸው ነውና የሚጠበቅ ነው። የአፍሪካ አምባገነኖች የራሳቸውን ቅዠትና ጨኸት ለራሳቸው እያዳመጡ ቅዠታቸውን ራሱ መልሰው ያምኑትና፣ ያን የጭንቀት ጨኸታቸውን ህዝብን አስገድደው እንዲለብሰው በማስደረግ "ሕዝባዊ ድጋፋችንን" እዩልን ብለው አረፋ ይደፍቃሉ፣ ያቅራራሉ፣ ይደነፋሉ። ወይ አለመታደል! ምን ይሉታል እንዲህ ዓይነቱን ዕብደት?

ወይ አልመታደል፣ ወይ አለመማር፤
ዝንብ ቆሻሻ ቀስማ፣ ሠራች አሉኝ ማር፤
የዝንብ ማር መሥራት፣ ባይገባኝ ምስጢሩ፤
የዝንቧን ጠጅ ጠጥተው፣ ያበዱ የሠከሩ፤
የቅንድቡን ማማር፣ የፀጉሩን ቁንጅና ወጥተው መሠከሩ።

ከሁሉም ከሁሉም፣ በጣም ያሰደመመኝ፤
የቅንድቡን ማማር፣ ገልጦ ከነገረኝ፤
የዓይኖቹን ሽፋሽፌት፣ ካወዳደሰልኝ፤
የጥርሱን ንቅሳት፣ ምነው አስቀረብኝ?

አዬ ጉድ አዬ ጉድ፣ የግርንቢጥ ዘመን፤
እኔ ለጠመንጃ ፣ "ቆንጅየው" ለዘፈን፤
ባትበሳጩብኝ፣ ባትቆጡብኝ፤
ስለ መቃ አንገቱም ግጥም ፃፍልኝ።

ባንዲራ ጨርቅ ነው፣ ብሎ የደነፋውን፤
ድንባዣም ወጠጤ፤ እበቀላለሁ ስል፤
ከአፉ ማር ጠብ ይላል፣ ብሎ ቢነግረኝ፤
ከተደበቀበት ሠንድቅ ዓላማዬን፣ ይዠ ቀርብኩኝ።

ወይ ሰለሞን ተካልኝ! ያዋልብህ አይጠቀም አቦ!።

የሕዝብ ትግል ያቸንፋል! የታሠሩ የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

ቸር ይግጠመን!

may 26/ 2010